ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር
KINIJIT NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS
(KNAASO)
766 Rock Creek Church Rd. NW. Washington DC. 20010
Tel: (202) 541 0556 Fax: (202) 541-0557 Email: kinijitna@kinijitna.org

# የእብሪት መጨረሻው ውድቀት ነው - ዴሞክራሲና ኢሕአዴግ

ባለፉት አሥራ ሰባት ዓመታት ራሱን በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ የጫነውን ኢሕአዴግን የሚገልጹ ሁለት ባሕርያት ጠቁሙ ቢባል በሰው ሕሊና ውስጥ ዘለው የሚመጡት “ፀረ-ዴሞክራሲነት” እና “እብሪት” ቢሆኑ አያስገርምም።

ኢሕአዴግ ዴሞክራሲን ከሺህ ጦር የበለጠ እንደሚፈራ ያለፉት አሥራ ሰባት ዓመታት ድርጊቶቹ በቂ ማስረጃዎች ናቸው። የሚቻል ቢሆን ዴሞክራሲ እና የሕዝብ አንድነት የሚባሉ ቃላቶች ከመዝገበ ቃላት ቢወገዱለት ደስታው ነው.... የሥልጣን መሠረቴን ያናጉብኛል ብሎ ሌት ተቀን የሚባንንባቸው፤ በአፈና፤ በግድያና በሺንገላ ብዛት ሊጠፉ የማይችሉ ክፉ ባላንጣዎቹ መሆናቸውን ያውቃልና!

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ መንግሥት ቆሞ የሚሄደው በውጭ እርዳታና በምጽዋት ብዛት ስለሆነ ኃያላን መንግሥታት ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ እንዲገነባና ሰብአዊ መብት እንዲከበር የሚያሳድሩበትን ጫና ለማስተናገድ የይስሙላ ምርጫዎችን ማካሄድ ብቻ በቂ ነው ብሎ የሚያምን ጉደኛ መንግሥት ነው።

ባለፉት ዓመታት ኢሕአዴግ ተወዳዳሪ፤ ኢሕዴግ ታዛቢ፤ ኢሕአዴግ ዳኛ፤ ኢሕአዴግ አሸናፊና ኢሕዴግ አስፈጻሚ የሆነባቸው ሦስት “ምርጫዎች” ተከናውነዋል። ሦስተኛውና የ97ቱ ምርጫ በዓይነቱም በይዘቱም ከሌሎቹ የተሻለ ብቻ ሳይሆን የውጭ ታዛቢዎች በርከት ብለው የተሳተፉበትና ዜጎች ታላቅ ተስፋ የጣሉበት ነበር። ውጤቱ ኢሕዴግ በጠበቀው መሥመር ሳይሆን ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለሥልጣን የሚያበቃ መሆኑን ሲገነዘብ ኢሕአዴግ ሰላማዊ ዜጎች ላይ ዘግናኝ የግድያ፤ የሥራትና የአፈና ፕሮግራም አካሂዶ የሕዝቡን ድምጽ አፈነ። ከዚያ ወዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተዳደረው በቀልንና ጥላቻን ያስተዳደር መመሪያው ባደረገ መንግሥት ሥር ነው ቢባል ማጋነን አይኖርበትም።

የሰሞኑ ምርጫ ተብዬ ደግሞ ዴሞክራሲን በብሩህ ገጽታው ለማየት የምንጓጓውን ብቻ ሳይሆን የራሱን የኢሕአዴግን ደጋፊዎች እንኳ የሚያሸማቅቅ፤ ዓይን ያወጣ ማታለልና እብሪት የተደባለቀበት የማናለብኞች ሥራ ነው። ታማኝ ተቃዋሚ የሚባሉት ፓርቲዎች እንኳ ምርጫው ኢ-ፍትሐዊ መሆኑን አይተው በተዋናይነት ላለመሳተፍ ወስነዋል። ከተሳሳተ የውጭ ፖሊሲ ተነስተው በተመጠነ ደርጃ ድጋፍ ሲሰጡ የነበሩ መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችም ቢሆኑ ከኢሕአዴግ ጋር ያላቸውን የሚቆረቁር ግንኙነት እንደገና እንዲመረምሩ የሚገፉፉቸው ሁኔታ ለመፈጠሩ ሹሞቻቸው በየጊዜው የሚሰጧቸውን መግለጫዎች ማየት ብቻ ይበቃል። ገበሬውን ማሳህን እነጥቅሀለሁ፤ ሠራተኛውንና አስተማሪውን በእንጀራህ እመጣብሀለሁ፤ ነጋዴውን ፈቃድህን እሠረዛለሁ እያለ የሚያስፈራራና የአባልነት ቅጽ የሚያስሞላ ፓርቲና መንግሥት ደሞክራሲያዊ አይደለም፤ ዘለቄታም አይኖረውም።

ኢሕአዴግ ከአንድ እብሪት ወደ ሌላ እብሪት እየተረማመደ ያለው ወታደራዊና የስለላ ኃይሉን ታምኖ ብቻ ነው። በኑሮ ውድነት፤ በፍትህ መዛባት፤ በጉቦኞነት፤ በመብት ረገጣ ቆሽቱ ያረረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያሳየው ጥርሱን እንጅ ልቡን እንዳልሆነ በ97 ምርጫ አይቶታል። አሁንም እያየው ነው። የአመጽ አለመኖርን እንደመረጋጋት፤ ዝምታን እንደ አመኔታ የሚቆጥር መንግሥት ዓይነ ህሊናው በእብሪት የተጋረደ ብቻ ለመሆኑ ታሪክ ደግሞና ደጋግሞ አሳይቶናል። ኢሕአዴግ ነፃ ፕሬሱን እያጠፋ፤ ለዴሞክራሲና ለፍትህ ማቆጥቆጥ አስፈላጊ የሆኑ መዋቅሮችን በመዳፉ ሥር እያደረገ፤ የተወዳዳሪ ፓርቲ አባላትና እጩዎች የሚንቀሳቀሱበትን የፖለቲካ አየር በማስፈራራትና በእሥራት እየበከለ፤ ፀረ ዴሞክራሲ ሕጎችን በየዕለቱ በነጋሪት ጋዜጣ እያወጀ፤ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አካሂጃለሁ እያለ ቢለፍፍ የሚያታልለው እራሱን ብቻ ነው። የሚያሳጥረውም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በፍቅር የሚያስተሳስረውን ገመድ ነው።

የሰሞኑ ምርጫ የ2002 ምርጫ ምን እንደሚመስል ከወዲሁ የሚያመላክተን ስለሆነ አጥብቀን እናወግዘዋለን። ኢሕአዴግ ከስህተቱ ለመማር ፈቃደኛነት የሌለው፤ ለደሞክራሲና ለመብት ደንታ የማይሰጥ፤ በእብሪት የተወጠረ መንግሥት መሆኑን በድጋሚ እያስመሰከረ ቢሆንም ለብሔራዊ እርቅ፤ ለሠላም፤ ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ከገባነው ጽኑ ቃል ኪዳን በመነሳት ኢሕአዴግ በዴሞክራሲ ላይ የሚያደርገውን አሳፋሪ ደባ ባስቸኳይ እንዲያቆም አጥብቀን እናሳስባለ።

በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የድጋፍ ድርጅቶችና መላ ሕብረተሰቡ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ውስጥ እስኪሰፍን ድረስ ዕውቀታችንን፤ ገንዘባችንንና ጊዜያችን መስዋዕት በማድረግ ከወገናችን ጎን እንደምንሰለፍ በድጋሚ እናረጋግጣለን።

ዴሞክራሲ ሊጨናገፍ የማይችል የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ነው!

ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር
ኤፕሪል 14 ቀን 2008 ዓ/ም